የሰ/መ/ቁ.16062

ህዳር 19 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
አብዱልቃድር መሐመድ
ሐጐስ ወልዱ
ዳኜ መላኩ
መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነገረፈጁ አቶ አብርሃም ፀጋዬ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ አልቀረበችም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ሊሆን የቻለው የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡

ይኼው ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ.304/92 በቀረበለት ካሳ ጉዳይ ላይ የአሁኑ አመልካች በጣልቃ ገብነት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን አድርጐ ጣልቃ ገቡ በፍትሐብሔር ህግ ቁ.2143/1/ መሠረት ያቀረበውን የይርጋ ክርክር በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ ግንቦት 21 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት በከሣሽ በኩል የቀረበውን ክሥና በግራ ቀኙ መካከል የተደረጉትን የፍሬ ነገር ክርክሮች መርምሮ ከሣሽዋ ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ ባለቤቷ አቶ ሀ/ሚካኤል መርጊያ ንብረትነቱ የአንደኛ ተከሣሽ በሆነው የሰሌዳ ቁጥር 3-17155 መኪና ተገጭቶ በመሞቱ ምክንያት በሚስቱና በሁለቱ ህፃናት ልጆቹ ላይ በቀለብ ረገድ ለደረሰው ጉዳት የመኪናው ባለቤት አንደኛው ተከሣሽ እና መኪናውን ሲያሽከረክር አደጋውን ያደረሰው ሁለተኛው ተከሣሽ በሕግ ኃላፊ ስለሚሆኑ ካሣ ብር 60,000 ሊከፍሉ ይገባል፡፡ ጣልቃ ገብ የሆነው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በበኩሉ ግጭቱን ላደረሰው መኪና በገባው የመድን ዋስትና መጠን ካሣውን መክፈል አለበት የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጣልቃ ገብነት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን የተደረገው የአሁኑ አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ባለመስማማትና ክሱም በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚል ምክንያት በፍ/ይ/መ/ቁ.03564 ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ሊያቀርብ የቻለ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ መጋቢት 14 ቀን 1996 ዓ.ም መርምሮ በሰጠው ትዕዛዝ ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም



በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.337 መሠረት ይግባኙን በመሠረዝ አሰናብቶታል፡፡

በዚህ መዝገብ ለሰበር አቤቱታ የቀረበውም ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ ጉዳዩን ተመልክቶ የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በሚል ሲሆን አመልካች በተነሣው የይርጋ ክርክር ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚልበትን ምክንያት ሰኔ 11 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አብራርቶ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ ተመርምሮ የይርጋው ጥያቄ ከሕጉ አኳያ ተጣርቶ መወሰን የሚያስፈልገው ሆኖ በመታየቱ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በአመልካች በኩል የቀረበው ማመልከቻም ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮ ቀርባ መልስ እንድትሰጥበት ታዞ በ15/4/97 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርባለች፡፡ በጽሑፍ ያቀረበችው መልስ ሲታይ ተጠሪ ባለቤቱ በመኪና ተገጭቶ በመሞቱ ምክንያት በክሱ የተጠየቀው የጉዳት ካሣ እንዲከፈል ሣይሆን በቀለብና መተዳደሪያ ረገድ ታስቦ ሊከፈለን የሚገባ ገንዘብ ነው፡፡ ክሱ በጉዳት ካሣ ጥያቄ ላይ ያልተመሠረተ ከሆነ ደግሞ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2143/1/ በመጥቀስ የሚያቀርበው የይርጋ ክርክር ሊኖር አይችልም፡፡ ስለዚህ ክሱ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ ሌላ በሚስትነት ጉዳይ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች በክርክር ላይ ቆይቼ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠው በ07/07/90 ስለሆነ ክሥ የማቅረብ መብት ያገኘሁት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ ደግሞ በ4/1/92 ያቀረብኩት ክሥ ከይርጋ ነፃ ነው የሚሉትን ክርክሮች ያቀፈ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ደግሞ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪ ክሥ ያቀረበችው አደጋው ወይም ጉዳቱ ከደረሰ ከሰባት አመት ቆይታ በኋላ ነው፡፡ የይርጋ ጊዜ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2143/2/ መሠረት ለወንጀሉ ጉዳይ የተወሰነው የይርጋ ዘመን ልክ ይሆናል ከተባለም አደጋውን ያደረሰው ሹፌር የወ/መ/ሕ/ቁ.526/1/ ተጠቅሶ ክሥ ቀርቦበት በብር 1000 የተቀጣ መሆኑ በማሥረጃ ስለተረጋገጠ ለዚህ ወንጀል የተወሰነው የይርጋ ጊዜ ሶስት አመት ብቻ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

ችሎቱም በቀረበው ጉዳይ በዋናነት ሊመረመር የሚገባው ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል አይሆንም? ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ ከተገኘ የይርጋው ዘመን ልክ ምን ያህል ነው የሚለው የይርጋ ጥያቄ መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ለመረዳት እንደተቻለው ከሣሽ የሆነችው የአሁኗ ተጠሪ ሁለተኛ ተከሣሽ የሆነው ከበደ ኃይሉ ንብረትነቱ የአንደኛው ተከሣሽ አሊ መሐመድ የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-17155 መኪና እያሽከረከረ ሲንዝ ሰኔ 5 ቀን 1984

ዓ.ም ባለቤቴ አቶ ሀ/ሚካኤል መርጊያን ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት ገጭቶ ገድሎታል በማለት በባለቤቷ መሞት ምክንያት እርሷ እና ሁለት ህፃናት ልጆቹ ቀርቶብናል ወይም አጥተናል የምትለውን ገንዘብ በመግለጽ አስልታ በጠቅላላው ብር 222,000 ተከሣሾች በአንድነት በነጠላ እንዲከፍሏት በ4/1/92 ዓ.ም ተጽፎ እንዲቀርብ ባደረገችው ክሥ ጠይቃለች፡፡ የአሁኑ አመልካች የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በቀጥታ የቀረበበት ክሥ ባይኖርም አደጋውን ላደረሰው መኪና የመድን ዋስትና ሰጥቷል በመባሉ ምክንያት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43/1/ መሠረት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን አመልካችም አደጋውን ላደረሰው መኪና የመድን ዋስትና  በተገባለት መጠን ካሣ የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት አምኖ ክሱን በማስመልከት የበኩሉን መልስ ሲሰጥ የይርጋ ክርክር አንስቷል፡፡ በኢንሹራንስ ምክንያት ካሣ እንዲከፍል የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ከተደረገ ኢንሹራንስ ገቢው ጉዳት ደርሳብኛል ብሎ በከሰሰው ሰው ላይ ሊያቀርብ የሚችላቸውን የሕግ ክርክሮች ማቅረብ ይችላል፡፡ አመልካች ሦስተኛ ወገን ሆኖ የክርክር ተካፋይ በሆነበት ጉዳይ ክሱን በመቃወም የይርጋ ክርክር ሊያቀርብ የቻለው በዚሁ ሁኔታ በመጠቀም ነው፡፡

የቀረበውን የይርጋ ክርክር በተመለከተም ጉዳዩ ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነትን የሚመለከት ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ መሆን አለመሆኑ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2143 አኳያ የሚመረመር ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለይርጋው ክርክር መነሻ ያደረገው ይኼው ከውል ከውል ውጭ ስለሚመለከት ካሣ ጉዳይ ክሥ የይርጋ ዘመን የሚወሰነውን ድንጋጌ ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገር ጉዳዩ ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነት የሚመለከት መሆኑን እያረጋገጠ ተጠሪዋ በአመልካች በኩል ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መልስ ስትሰጥ ጉዳዩ ሟች በመኪና ተገጭቶ ከመሞቱ ጋር የተያያዘ ቢሆንም ክሱ የተመሠረተው በቀለብ ጥያቄ ላይ እንጅ በጉዳት ካሣ ላይ ስላልሆነ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2143 ላይ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም በሚል ያቀረችው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ተጐጂው በመሞቱ ምክንያት ሚስት ወይም ልጆች በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2095 መሠረት በቀለብ መተዳደሪያ ረገድ የሚያቀርቡት የካሣ ጥያቄም ቢሆን ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነትን የሚመለከት እንጂ በሌላ የተለየ ግንኙነት ላይ ወይም በሌላ የሕግ ምክንያት ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡

በዚሁ በተጠቀሰው የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2143 ላይ የተመለከተው የይርጋ ዘመን ሲታይ የመጀመሪያው ንዑስ ቁጥር «1» ተበዳዩ ክሥ ማቅረብ



የሚችለው ካሣ የሚጠየቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት አመት ድረስ መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ የይርጋ ዘመኑ ርዝመት የበለጠ እንደሆነ የካሣው ጉዳይ ክሥ የይርጋ ዘመኑ ርዝመት እንደሚሆን ይገልፃል፡፡

የቀረበው ጉዳይ ከዚሁ የይርጋ ድንጋጌ አንፃር ሲመረመር የአሁኗ ተጠሪ ካሣ የተጠየቀበት ጉዳት ሰኔ 5 ቀን 1984 ዓ.ም ደርሶ የካሣውን ጉዳይ ክሥ ያቀረበችው መስከረም 4 ቀን 1992 ዓ.ም መሆኑ ስለተረጋገጠ በሕጉ የመጀመሪያ ንዑስ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው ሁለት አመት የይርጋ ዘመን ያለፈው የመሆኑን ጉዳይ አከራካሪ ሊሆን አይችልም፡፡ የሚቀረው ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ ከተገኘ በወቅቱ በነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተመለከተው የይርጋ ዘመን ምን ያህል ይሆናል? በዚህ ሕግ መሠረት ቢታይ የይርጋው ዘመን አላለፈም ሊባል ይችላል አይችልም? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ አደጋ ያደረሰውን መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሾፌር ሁለተኛው ተከሣሽ በዚህ ጉዳይ ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት በመኪና ሰው ገጭቶ ገድሏል ተብሎ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526/1/ ተጠቅሶ በቀረበበት የወንጀል ክሥ ፍ/ቤት ጥፋተኛ መሆኑን አረጋግጦ በገንዘብ መቀጫ ብር 1000 እንዲቀጣ መወሰኑ ተገልጿል፡፡ ሾፌሩ በወንጀሉ ጉዳይ ተከሶ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣበት የሕግ አንቀጽ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 526/1/ መሆኑ ከታወቀ የወንጀሉ ጉዳይ የክሥ አቀራረብ የይርጋ ዘመን ምን ያህል ጊዜ ነው የሚለውን በተመለከተ ከወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 226 በመመልከት ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚ ነው ለማለት የተቻለው የይርጋ ዘመን በዚሁ በተጠቀሰው ሕግ ፊደል ሠ ላይ የተመለከተው አምሥት አመት ነው፡፡

የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ ክሱን ያቀረበችው ጉዳቱ በደረሰ በአምሥት አመት ጊዜ ሣይሆን ከሰባት አመት ቆይታ በኋላ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ሚስትነቴን እስካስወሰን ድረስ በክርክር ላይ የቆየሁት ጊዜ መታሰብ የለበትም፣ ክሥ የማቅረብ መብት ያገኘሁት ሚስትነቴን ካስወሰንኩ በኋላ ስለሆነ የይርጋው ጊዜ መታሰብ ያለበት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው በሚል ያቀረችው ክርክር በሕግ ተቀባይነት የለውም፡፡ በፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 2143/1/ ላይ እንደተመለከተው የይርጋው ጊዜ የሚቆጠረው ካሣ የሚጠየቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ መዘግየት የጠቀሰችው ምክንያት በሕጉ ይርጋውን የሚያቋርጥ ወይም የሚያረዝም አይደለም፡፡

ክሱ የቀረበው በወንጀሉም ጉዳይ የተወሰነው የይርጋ ዘመን ካለፈ በኋላ ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ሆኗል። አንድ ተከራካሪ ወገን በሕግ ይገባኛል የሚለውን መብት በሕጉ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ካልጠየቀ በሕግ ከሶ የመጠየቅ መብቱ ቀሪ ይሆናል። የአሁኗ ተጠሪም በባለቤቷ መሞት ምክንያት በሕግ ይገባኛል የምትለውን ካሣ በሕጉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ክሥ አቅርባ ስላልተጠየቀች ካሣ የመጠየቅ መብቷ ቀርቷል።

በዚህ ምክንያት በቀረበው ጉዳይ ክሱ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በሚል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል።

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ በማስመልከት በ21/9/1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔም ሆነ የኦሮሚያ ጠቅላይ በመ/ቁ.03564 - በ14/7/96 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/348/1/ መሠረት ተሽሯል።
2. በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።

በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሣኔ ትክክለኛ ግልባጭ ይተላለፍ ጉዳዩ ስለተወሰነ መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



የሰበር መ/ቁ.14554

ታህሣስ 20 ቀን 1998 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አቶ ከማል በድሪ
2. አቶ ፍሰሀ ወርቅነህ
3. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
4. ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ፅጌ አጥናፌ

**መልስ ሰጭ፡-** ባለምባራስ ውቤ ሺበሺ

ተዋዋይ ወገን ሳይሆን ውል እንዲሠረዝ ስለመጠየቅ በአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ፍ/ቤት የመሠረዝ ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1808/2/፣ 1198/2/

ካለ አመልካች ፈቃድ የጋራቸው የሆነውን ቤት ስም ለማዛወር አመልካች ባለቤት ተከጠሪ ጋር የፈፀመው ውል ፈራሽ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መወሰኑና የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሉ እንዲፈርስ አመልካች የጠየቁት ያለአግባብ ነው በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻሩ በመጨረሻም የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔውን በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡-

<u>ውሳኔ</u>፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሠሰው ትዕዛዝ ተሽሯል።

1. ተዋዋይ ወገን ሳይሆን በተፈፀመ ውል ምክንያት መብቱ ተነክቷል በማለት ውሉ እንዲሰረዝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም ምክንያት ከህግ ውጭ ከሆነ፣ ለህሊና ተቃራኒ ወይም ለውል አፃፃፍ የተደነገገው ፎርም አልጠበቀም በሚል ምክንያት ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ የሚቀርብ ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም።
2. የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የመሠረዝ ሥልጣን ደብተሩን የሰጠው የአስተዳደር አካል እንጅ የፍ/ቤት አይደለም።
3. በአስተዳደር ክፍሉም እስካልተሰረዘ ድረስ የደብተሩ ባለቤት የቤቱ ባለንብረት እንደሆነ ይቆጠራል።